# በምርምር ዉስጥ ለመሳተፍ አጭር የስምምነት ቅጽ

በምርምር ጥናት ውስጥ እንዲሳተፉ እየተጠየቁ ነው። ወደጥናቱ ለመግባት ከመስማማትዎ በፊት መረዳት በሚችሉት ቋንቋ ግልጽ የሆነ ማብራሪያ ማግኘትዎ አስፈላጊ ነው። የሚከተለዉ ይህንን የስምምነት ቅጽ ሲፈርሙ የሚስማሙባቸዉ ነገሮች ዝርዝር ነዉ።

ጥናቱን ከሚያካሄዱ መርማሪዎች አንዱ ወይም ከተወካዮቻቸዉ አንዱ የሆነ አስተርጓሚ ስለሚከተሉት አስረድቶታል:

1. አላማዎች፣ ሂደቶቹን፣ እና ምርምሩ ምን ያክል ጊዜ እንደሚቆይ፤
2. በሙከራ ላይ ያሉ ማንኛቸውም ሂደቶች፤
3. ማንኛዉም በምክንያታዊነት ሊጠበቁ የሚችሉ አደጋዎች (በዚህ ጊዜ የሚታወቁ ሊፈጠሩ የሚችሉ አደጋዊች)፣ የምርምሩን አለመመቸቶች እና ጥቅሞች
4. ማንኛውም ጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ አማራጭ ሂደቶች ወይም ህክምናዎች፤ እና
5. ሚስጢራዊነት እንዴት እንደሚጠበቅ።

ለዚህ ጥናት ሲጠቀስ፣ ስለሚከተሉት ተነግሮዎታል፡

1. በምርምሩ ወቅት ጉዳት ከደረሰብዎት ማንኛዉም ሊገኝ የሚችል ማካካሻ ወይም ህክምና፤
2. ያልተጠበቁ አደጋዎች የመኖራቸዉ ዕድል (በዚህ ጊዜ የማይታወቁ አደጋዎች)፤
3. መርማሪዉ ተሳትፎዎን ሊያቆም የሚችልባቸዉ ሁኔታዎች፤
4. ማንኛዉም በእርሶ ላይ የሚጨመሩ ወጪዎች፤
5. መሳተፍ ለማቅም ቢወስኑ ምን እንደሚፈጠር፤
6. የመሳተፍ ፈቃደኝነትዎ ላይ ተጽእኖ ሊፈጥሩ ስለሚችሉ አዳዲስ ግኝቶች መቼ እንደሚነገርዎ፤ እና
7. በጥናቱ ዉስጥ ምን ያህል ሰዎች እንደሚኖሩ።

ስለጥናቱ እና ስለ አላይና ጤና ተቋማዊ ግምገማ ቦርድ አስተዳደር ቢሮ (Allina Health Institutional Review Board Administration Office) ጥያቄዎች ወይም ችግሮች ካጋጠምዎት በ612-262-4920 እንደ የምርምር ተሳታፊ ስለመብትዎ፣ ስለ የምርምር ጥናቱ ወይም ቢጎዱ ምን ማድረግ እንዳለብዎት ማንኛዉም ጥያቄዎች ካሉዎት በ___________________ ዋና መርማሪ(PI) _________________መገናኘት እንደሚችሉ ተነግሮዎታል።

በዚህ ምርምር ዉስጥ ተሳትፎዎ በበጎ ፈቃደኝነት እንደሆነ እና ለመሳተፍ ፈቃደኛ ባይሆኑ ወይም ለመሳተፍ ከተስማሙ በኋላ ለማቆም ቢወስኑ እንደማይቀጡ ወይም ጥቅሞችን እንደማያጡ ተነግሮታል።

ለመሳተፍ ከተስማሙ፣ የዚህን ሰነድ የተፈረመበት ቅጂ እና የምርምሩን የጸሁፍ ማጠቃለያ በእንግሊዝኛ ቋንቋ እንደሚሰጥዎት ተነግሮታል።

ይህንን ሰነድ መፈረም ማለት የምርምር ጥናቱ፣ ከላይ ያለዉን መረጃ ጨምሮ፣ በቃል ተገልጾሎታል እናም በበጎ ፈቃደኝነት ለመሳተፍ ተስማምተዋል ማለት ነዉ።

____________________________________________ _______________

የተሳታፊ/ህጋዊ ፈቃድ ያለዉ ተወካይ/ዘመድ ፊርማ — ቀን እና ሰዐት

____________________________________________ _______________

የምስክር ፊርማ — ቀን እና ሰዐት

Amharic